መስከረም ፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን።**

የተከበራችሁ አባቶቼና እናቶቼ ወንድሞቼና እህቶቼ ሕፃናት በሀገራችን በኢትዮጵያና በአለንበት ሀገር በሰሜን አሜሪካ በልዩ ልዩ ዓለማት የምትገኙ ወገኖቼ በሙሉ ከሁሉ አስቀድሞ የዘመናት ባለቤት የምሕረት አምላክ የሰላም አባት ስሙ የተመሰገነ ይሁንና በረድኤት ጠብቆ እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደዘመነ ሉቃስ በሰላምና በጤና አሸጋገራችሁ አደረሳችሁ እያልኩ ዘመኑ የህይወትና የጤና የፍቅርና የክብር የእድገትና የብልጽግና የምግባርና የሃይማኖት ዘመን እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቴን በዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ስም ስገልጽ በታላናቅ ትህትና ነው።

በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኛችሁ ወገኖቼ

**"የሚመጣውን ዘመን ልብ አድርጉ የእግዚአብሔር መቅደስ መሠረት ከተተከለበት ቀን ጀምሮ ልብ አድርጉ … ከዚች ቀን ጀምሮ እባርካችኋለሁ"** ትንቢተ ሐጌ ፪፡ ፲፰-፲፱

በአዲሱ አመት በርከትን ለመቀበል የእግዚአብሔር ሰው መሆን ግድ ይላል ከዘመን ወደ ዘመን ስንሸጋገር ያሳለፍነውን ዘመንም ሆነ የምንቀበለውን ዘመን ከማንነታችን ጋር በማነፃፀር ከክፋት ወደ በጎነት ከኃጢያት ወደ ጽድቅ በመመለስ ለንስሐና ለበረከት የሚገባ ፍሬ ማፍራት ሌላው ትልቅ እድል መሆኑን ልብ ልናደርገው ይገባል።ዘመን መልካም ሥራ ቢሠሩበት በሰውም ይሁን በእግዚአብሔር ፊት ተወዳጅነትን ያስገኛል። ክብርና ሞገስም ያሰጣል። በአንፃሩም ክፉ ሥራ ቢሠሩበት በየትኛውም ወገን ያስወቅሳል መርገምንም ያስከትላል። በሁሉም ዙሪያ በረከት የለሽ ያደርጋል።

**"ልብ አድርጉ"** በሚለው ቃል የነቢዩን ትንቢት ስንመለከት በዘመኑ ከአምልኮቱም ከምግባሩም የራቁ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው ግድ የማይሰጣቸው ሰዎች ተፈጥረዋል። ከክፉ ሥራቸውም የተነሳ ብዙ ዘርትው ጥቂት የሚሰበስቡ በልተው የማይጠግቡ ጠጥተው የማይረኩ ለብሰው የማይሞቃቸው ደመወዝ ተቀብለው በቀዳዳ ከረጢት የሚጨምሩ ከበረከት የራቁ ሆነው ነበርና በተሰጣቸው ዘመን ከክፉ ሥራቸው ተመልሰው ንስሐ ገብተው እንዲኖሩ ማንነትን በሚጠይቅ ልብን በሚነካ አፅምን በሚሠብር ኃይለቃል በመገሠጽ የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ ነቢዩ ሐጌ ነግሮአቸዋል።ለቤተ

እግዚአብሔር ሥራ ቀናተኞች እንዲሆኑ መልካም ሥራ እንዲሠሩ የፈረስ እንዲያድሱ በማስተማር ለክብር ጠርቶአቸዋል።ይህን የመሳሰለውን መልካም ሥራ እስከ ሠሩም ድረስ **"ከዚች ቀን ጀምሮ እባርካችኋለሁ"** ይላል እግዚአብሔር በማለት ፍቅርና ርኅራኄ የተመላበትን የአምላካችንን የምሥራች ድምፅ አሰምቷቸዋል።

ጥሪው ከማዳን ሥራው ጋር ቀጥሎ የራቀውን በማቅረብ ዓመተ ፍዳን በማስወገድ ዓመተ ምሕረትን ሰጥቶናል። ሁላችንም በብርሃን መኖርና መመላለስ እንድንችል አምላካችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቸርነቱ ብዛት የተነሳ መርገምን አስወግዶ በልዩ በረከት ባርኮናል። ይሁን እንጂ አንዳንዶች በዓለም ፍላጎትና ምኞት በመሳብና በመጎተት አልፎ ተርፎም በመማረክ ያልተሰጣቸውን በመሻት የነርሱ ያልሆነውን በመፈለግ በእከብር ባይነት የነገሮችን ከንቱነት ልብ ባለማድረግ ለክብርና ለበረከት ይልቁንም ለንስሐ የተሰጠውን ዘመን ሳይጠቀሙበት ከዘመኑ ጋር ተፋጠዋል። እኛነታችንንም ያለአድልዎ ልብ አድርገን ስናየዉ ከተጠቀሱት ሰዎች የራቅን ነን ማለት አያስደፍርም።

ርዕሰ ዓውደ ዓመቱን ስናከብር ልብ ልናደረው የሚገባን እንደ አባቶቻችን በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበን በዝማሬ በቅዳሴ እግዚአብሔርን በማመስገን ሥርዓቱን ተከትለን እውነተኛ አምልኮት ስንፈጽም ብቻ ነው። ከዚህም ጋር ፍሬ ግብሩን አሥራት በኵራቱን አቅርበን በረከት መቀበል የአማኝነት መስፈርታችን ነው። ከዚህ ውጭ በስም ክርስቲያን በግብር ሲሞንአዊ ሆኖ መታየት ውድቀት ነው።

**"ከብዙ ዘመን ጀምሮ በጥንቆላ ስላስገረማቸው ያዳምጡት ነበር"** የሐዋ ሥራ ፰፡፲፩ ሲሞን የተባለው መሰሪ ብዙወችን አስገርሞአል ቅዱሳን ሐዋርያትንም በገንዘብ በማታለል መንፈስ ቅዱስን ለመግዛት አስቦአል። ሲሞን በግብር የወለዳቸው ልጆች በዘመናት ሁሉ ልበ ቢሶችን ማስተዋል የተሳናቸውን በምትሐት ወይም በማስመሰል ሲያስገርሙ ኖረዋል። ዛሬም ላይ ሰለጠነ በተባለው ዓለም ሳይቀር ሲያስገርሙና ሲያታልሉ ይኖራሉ። አስገራሚዎቹም ተገራሚወቹም ልብ ባለማለት ከክርስትና ጋር የማይዛመዱ ተግባራትን ያከናውናሉ።ስለዚህ በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ የነዚህ ግብር ተካፋይ የሆነ ማንኛውም ስመ ክርስቲያን የግብር ክርስቲያን በመሆን ካላስፈላጊ ቁራኛ ከእግዚአብሔር ከሚለይ ክፉ ደዌ በአዲሱ ዘመን በንስሐ ሊገላገል ይገባዋል።ለመገላገልም **"ልብ ማድረግ"** አለበት። አንድ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን በኑሮው ሁሉ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በፈጣሪው ቸርነት በቅዱሳኑ ተራዳኢነት በወላዲተ አምላክ አማላጅነት ከማንኛውም አምልኮ ባዕድ ተላቆ ክርስቲያን ብቻ መሆን አለበት። ሰውን ወዶ ፍቅር ስቦት ወደዚህ ዓለም የመጣው ዘመን የማይቆጠርለት ዘመናትን የሚቆጥር ጥንትም ያለ ወደፊትም የሚኖር "ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው፡ "የዘመናት

ባለቤት **“ወደኔ ቅረቡ ይህንንም ስሙ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርኩም ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርኩ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል”**።ኢሳ ፵፰፡ ፲፮ ከኃዘን ወደደስታ ከመከራ ወደእረፍት ከኃሳር ወደ ክብር ከድንቁርና ወዕደውቀት እመልሳችኋለሁ። ሲል ጥሪውን ያስተላልፋል። ስለሆነም አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን የሚያሰኘውን ተግባር በመፈጸም ጠሪውን ሰምቶ እግዚአብሔርን አውቆና አምኖ ትእዛዙን ጠብቆ ሲገኝ በእውነት ክርስቲያን ይባላል።ለራሳቸው በማያውቁ ሰዎች በተፈጠረ የማታልያ ስልት ተሳስቶ ለንስሐ በተሰጠው ዘመን ልብ ማድረግን ረስቶ ሲወድቅ ሲነሳ እስከተገኘ ድረስ ልብሰ ክርስቲያን ስመ ክርስቲያን መባሉ የማይቀር ነው። የእግዚአብሔርንም ትግስት ይፈታተናል።

**“ከድሮ ዘመን ጀምሮ ዝም ብያለሁ ዝም ብየም ታግሻለሁ”**ኢሳ ፵፪ ፡፲፬ አምላካችን እግዚአብሔር አይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆን ዘመኑን ሲሰጠን ሰዎች ልብ ማድረግ ይጠበቅብናል። ምክንያቱም ዝምታውና ትግሥቱ ከፍቅሩ ጽናት የተነሳ ልጆቹ እንሆን ዘንድ በንስሐ ለማቅረብ እንጂ በሥራዎቻችን ሁሉ በመስማማት አይደለም።

ስለዚህ በተሰጠን አዲስ አመት ከመነቃቀፍና ከመተቻቸት በመነጋገርና በመግባባት የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት እንጠብቅ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን መሠረት አድርገን በታሪካችን በሃይማኖታችን ኀፀጽ ጉድለት እንዳይገኝበት ስንዴው ከንክርዳዱ እንዳይቀላቀል የየድርሻችንን እንወጣ። **“ሁሉም በአግባብና በሥራት ይሁን”**። የቤተ መቅደሱ መሠረት እንዳይናወጽ አባቶቻችንና እናቶቻችን መስዋዕትነት ከፍለውበታልና ነገሮችን ሁሉ በዋዛ ፈዛዛ አንያቸው። ቤተ መቅደስ ሰውነታችን ለአምላካችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ማደሪያ ይሆን ዘንድ በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ጸንተን በምግባር ታንጸን የመንግሥቱ ወራሾች እንድንሆን ልብ ማድረግን ይስጠን።

ሁላችሁንም እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

የሰላም አምላክ ዘመኑን የበረከት የሰላምና የአንድነት ዘመን ያድርግልን በድጋሜ እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ለዘመነ ሉቃስ አደረሳችሁ።አምላከ አበው ለሀገራችን ለኢትዮጵያና ለመላው ዓለም ሰላሙን ይስጥ ይህችንን የምንኖርባትንም ሀገር ምድረ አሜሪካን በረድኤት ይጠብቅልን።

አባ አብርሃም

የዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ